# ትግላችን ዜና

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

Prepared by the Ethiopian Students Union
in Europe

P.O.Box 3198, 10364 Stockholm 3 SWEDEN

# ማጭበርበር ይበልጡን ያጋልጣል!

VOL. 5 Dec. 77 ለዩ እትም

Special Issue ህዳር ፲፱፻፸

ይዘት


- ማጭበርበር ይበለጡን ያጋልጣል! . . . . . . 1
- የመላው ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር
  የሸዋ ክፍለ ሀገር ገበሬዎች ማህበር
  የአዲስ አበባ አጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር
  ከጥቅምት 14 እስከ ጥቅምት 17 1970 ዓ.ም.
  የተካሄደው ስብሰባ መግለጫና ውሳኔ . . . . . 8
- ከ ታጋይ ወዝአደሮች
  ለ የመላው ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር /መኢሠማ/ .15




## ማጭበርበር ይበለጡን ያጋልጣል!

የኢትዮጵያ አብዮት "ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት" እንደመሆኑ መጠን የዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄ አብይ ከሆኑት የዚህ አብዮት ጥያቄዎች አንዱ ነው:: በዚህ አብዮት ውስጥ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚታገለውና የሚሰዋው አብዮቱን ከግቡ አድርሶ የሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች ያለአንዳች ገደብ የሚከበሩበት ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ለመመሥረት ነው:: ነገር ግን ዲሞክራሲ እንደትግል ውጤትና ግብ ብቻ የሚወሰን ነገር እንዳይደለም ግልጽ ነው:: ዲሞክራሲ የትግል መሣሪያም ነው:: ሕዝቡ አብዮቱን ከግቡ ለማድረስ መንቃት፣ መደራጀትና መታጠቅ አለበት:: የዲሞክራሲ መብቶች ያለአንዳች ገደብ መለቀቅ ለንቃት፣ ለድርጅትና ለትጥቅ ለሚደረገው ትግል አመቺ ሁኔታ እንደሚፈጥር ጥርጥር የለውም:: የነዚህ መብቶች መስፋት የሕዝቡን አንድነት እንደሚያፋፍመው፣ የነሱ መታፈን ደግሞ ለአድሃሪዎች የማጭበርበሪያ ፋታ ሰጥቶ አብዮቱን ወደ ክስሳሀይነት እንደሚያወርደው ሊሳው ቢቀር ያለፈው ዓመት ትግላችን ያሳየን ሃቅ ነው::

በዲሞክራሲ መብቶች መለቀቅ ጉዳይ ዛሬ የተያዘው ክርክር ባንድ በኩል ለብሔራዊ ዲሞክራሲ አብዮት ታማኝ ሆነው ወደፊት በሚራመዱ ኃይሎችና በዚህ ፕሮግራም በመንሸራተት ከደርግ ጋር ወደ ቀኝ በመርገጥ ላይ ያሉ የቀኝ አድርባዮች ማካከል እንደሆነ ግልጽ ነው:: በተጨማሪም ለነዚህ አፍን የሚይዎሉ የቀኝ አድርባዮች ዛሬ "ቀን የወጣላቸው" ቀበሌቻው አቋማቸውን ለፍርፋሪ በሸጠም ዛሬ የሚከራከሩት ከብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ጋር ብቻ አይደለም:: ራሳቸው የዛሬ ሰደበት ወር ያስተጋቡት ከነበረው አብዮታዊ አቋም ጋርም መጣላ የያዙ መሆናቸው የዚያኑ ያህል ግልጽ ነው:: ዲሞክራሲ ለማን ? ለሚለው ጥያቄ ፕሮግራሙ፣ ማህበራችን፣ አብዮታዊያንና በጠቅላላው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ "ዲሞክራሲ ለጭቁኖች ያለአንዳች ገደብ" ይላሉ:: እንደዚህ አድርባይነቶቹ ድርጅቶች ደግሞ ለአድሃሪው ቢሮክራሲ የሰፊውን ሕዝብ መብቶች ማፈና ሕጋዊ ቀዳዳ ለመስጠት ዲሞክራሲ ለጭቁኖች ተገድቦ መሰጠት አለበት ይላሉ:: ዲሞክራሲ ለምን ? ሲባል ፕሮግራሙ፣ ማህበራችን፣ አብዮታዊያንና ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ "ለመንቃት፣ ለመደራጀትና ለመታጠቅ የሚደረገው ትግል የሠመረ ውጤት እንዲሰጥ" ብለው አቋሙን ይናገራሉ:: እንደዚህ አድርባይነቶቹ ለፍርፋሪ ያደሩ የቀኝ አድርባዮች ግን ዲሞክራሲ ተገድቦ ለጭቁኖች የ"የሚሰጠው" ነቅተው፣ ተደራጅተው፣ ታጥቀው የወዝአደር ፓርቲ ከቋቋሙ በኋላ መሆን አለበት በለው በኢትዮጵያ ጭቁኖች ላይ የሲያድ ባሬውን አይነት "የወዝአደር ፓርቲ" በሕዝቡ ትከሻ ላይ ለመጫን እየተሯሯጡ ናቸው:: ዲሞክራሲ መቼ ? በሚለው ጥያቄ ፕሮግራሙ፣ ማህበራችን፣ አብዮታዊያንና ሰፊው ሕዝብ ባጣዳፊ፣ ባስቸኳይ፣ አሁኑኑ እያሉ የዲሞክራሲያዊ መብቶችን አጣዳፊነት ያስገነዝባሉ:: የዛሬ ሁለት ዓመት ሲታወጅ ረቂ የነበረው፣ እነዓለማየሁ ኃይሌ አፍነውት ነበር

የተባለው፣ ጥር 27 ቀን ሌ/ኮ መንግሥቱ ኃይለ ማሪያም በቀርቡ ይታወቃል ያሉት የዲሞክራሲ አዋጅ ይታወጅ ይላሉ:: እንደሚሊሪድ አይነቶች ለፍርፋሪ የተሸጡ እፍኝ የማይሞሉ አድርባዮች እስከ ግንቦት ወር 1969 ዓ.ም ድረስ ከአብዮታዊያን ጋር ሆነው አሁኑኑ ሲሉ ከቆዩ በኋላ ዛሬ ይህን መፈክር "ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ይውደም" እንደሚለው አይነት የረጅም ጊዜ የፕሮፓጋንዳ መፈክር ነው በማለት የሰፊውን ሕዝብ የመብቶች ጥያቄ ለዘንተዓለም በቀጠሮ በማስተላለፍ ላይ ናቸው ።

ባጭሩ በዚህ በዲሞክራሲ ጥያቄ ላይ በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ የአብዮት ፕሮግራም ባንዲራ ስር የተሰለፉ፣ ለዚህ ፕሮግራም ሲታገሉ የወደቁ ጓደኞችን አርማ ያነሱ አርሶአደሮች፣ ወዛደሮች፣ መለዮ ለባሾች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አገር ወዳድ መኮንኖችና አብዮታዊያን ሁሉ ለዲሞክራሲያዊ መብቶች እየታገሉና እየሞቱ ናቸው:: በሌላ በኩል ግን ቡስቱ የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ጠላቶች፣ፀረ ዲሞክራሲ ጨለማ በደበበ ክፍላተ አገራት በስመ ሰርጎ ገብ ታጋይ ጓደኞችንና የጭቁን ብሄረሰቦች ታጋዮችን መጨፍጨፍ የያዙት ትምክህተኞች፣ አድሃሪው ቢሮክራሲ፣ ደርግና የቀኝ አድርባይ ምሁራን... ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዳይለቀቁ እየተፍጨረጨሩ ናቸው::

በፀረ ዲሞክራሲው ሰፈር፣ በተለይም ጊ.ወ.መንግሥትና አድሃሪው ቢሮክራሲ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በፈጠረት ፀረ ሕዝብ ሕብረት እየተጋገዙ ቀጥር ነፍስ ገዳዮችን ከእስር መልቀቅና በነሱ ቦታ ለዲሞክራሲ የሚታገሉትንና የሕዝብ ልጆች፣ ከብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ጋር ወደፊት የሚሉ ታጋዮችን በማሰርና በማንገላታት ላይ ናቸው:: እሰፍ አሰፍም በተለይ ትምክህተኞች ባገሰራረባቸው የደበበ፣ የደበበ ምስራቅና የደበበ ምዕራብ ክፍላተ አገራት ታጋይ ጓዶች በገፍ መረሸን ጀምረዋል:: ደርግና አድሃሪ ቢሮክራሲ በዚህ መልክ በፀረ ሕዝብ አመጽ ተሰማርተው ሊገቱ ያልቻሉትን ሕዝባዊ ትግል በለፍለፍ የቀኝ አድርባዮች አማካኝነት በማካሄድ "የመስመር ትግልም" ለመፈታተን እየተፍጨረጨሩ ናቸው:: የቀኝ አድርባዮች ግን ያልተገነዘቡት አንድ ሃቅ አለ:: በነሱ "ክርክር" ሰፊው ሕዝብ ለመብቱ የሚያደርገውን ትግል አያቆምም:: ከዚህ "ክርክር" የሚያተርፉት ነገር ቢኖር ከብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መንሸራተታቸውን ማጋለጣቸው እንደሚሆን ካሁኑ ማረጋገጥ ይቻላል:: ምክኒያቱም ሰፊው ሕዝብ፣ ማህበራችንና አብዮታዊያን ልጆቹ የሚከራከሩትና የሚዋደቁት "ስሉ" ያሳቸው እለት ከአንገላቸው በሚያፈልቋቸው መፈክሮች ሳይሆን ለዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መከበር ነውና ።

የቀኝ አድርባዮች ግን "ከርእዮተዓለሙ ግንባር" መፍረክረካቸውን አለተውም:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታእምር እየታዘበን ነው:: የቀኝ አድርባዮች ለፕሮግራሙ ታማኝ በመሆን ከደርግ ጋር ወደቀኝ አበረ አሰረገጥም ያለውን የማህበራችንን አቋምና በጠቅላላው አብዮታዊያንን "አድሃሪ"፣ "ከሃዲ" ማለት ጀምረዋል::"ያበዱን አከከ ወደ እምዬ" እንዲሉ:: የቀኝ



አድርባዮች ማርክስንና ሌኒንን አያወላጋግዱ አየጠቀሱ እንዴት ዲሞክራሲ "ከቋ" እንዳለ፣ እንዴት ባሁኑ ጊዜ "መቅረብ የሌለበት" ጥያቄ እንደሆነ ... ለማስረዳት በማርክሲዝም ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ፣ ምን አድርባይ ቢሆን ማንም አድርባይ በታሪክ ያላሳየውን አድርባይነት እያሳዩ ናቸው:: የቀኝ አድርባዮች በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ የዛሬ ዓመት ተኩል ባጣዳፊ፣ ባስቸኳይ የጊዜው ጥያቄ ተብሎ የነበረውን የዲሞክራሲ ጥያቄ "አሁኑኑ" ብሎ መጠየቅ እንዴት "አድሃሪነት" እንደሆነ ለማስረዳት እየተፍጨረጨሩ አበዩት ያህል ቁም ነገር ለፍርፋሪ የሸጡበትን ተለአክ እየፈጸሙ ናቸው::

ነገር ግን በማህበራችን አቋምና በጠቅላላው አብዮታዊያን ላይ የከፈቱት ይህ አይነቱ አሳፋሪ ዘመቻ በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የባሰውን ያጋለጣቸዋል እንጂ ጭቁኖቹን በአድሃሪው ቢሮክራሲ በነፍጠኞችና በትምክህተኞች በኩል እንደማያስለፍላቸው ግልጽ ነው:: ለምን? ምክኒያቱም ሰፊው ሕዝብ ለዲሞክራሲያዊ መብቶቹ ትግሉን ያፋፋመው ማርክስንና ሌኒንን ከዳር እስከዳር አንብቦ ስለተረዳ አይደለም:: ከእለታዊ ትግሉና ችግሩ፣ ለአብዮቱ መገፋት የግድ ዲሞክራሲ የተባለው የትግል መሣሪያ እንደሚያስፈልገው በመረዳቱ ነውና ።

የሆነ ሆኖ ደርግና አድሃሪው ቢሮክራሲ በቀኝ አድርባዮች ለፍለፋ ክርክር ረቶ መሄድ እንደማይቻል የተገነዘቡ ይመስላል:: ባለፈው ሰሞን አብዮታዊያን እንደ ሊህአፓ ቀጥረኞች ክርክር ፈርተው ይሸሻሉ በሚል የታሰባት ግምት በውንፋታ ክርክር በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዲጀምር ደርግ አዘዘ:: ክርክሩ ተጀመረ:: ትንሽ ሳይቆይ የአድርባዮቹ ውርግርግ አቋም እየተውረገረገ የማህበራችንና የአብዮታዊያን አቋም በጥራት እየጎላ መጣ:: ያደረሰት ምስኪኖች መለፈስለፍ ያልጣመው ደርግ ያአብዮታዊያንን አቋም የሚያንፀባርቁ ጽሑፎች በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳይወጡ ከለከለ:: ለምሳሌ "ታጋይ ለዲሞክራሲ አድርባይ ለፍርፋሪ" የሚለው /አዲስ ዘመን ሕዳር 7–8 1970/ አብዮታዊ ጽሑፍ አድርባዮች ሳወጡት አንድ ቡትቶ ትንተና ተገቢ መልስ መስጠት እንደጀመረና ሁለት ቀን እንደሄደ "ይቀጥላል" እንዳለ ተንጠልጥሎ እንደቀረ ተደርጓል:: ቀደም ሲል ሕዳር ስድስት ቀን "ታጋይ ሕዝብ ዲሞክራሲ ለጥቂቶች ያለገደብ አሁኑኑ" በሚል ርእስ ስር "ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ጋር ወደፊት ጥናት ነበብ" ባቀረበው አብዮታዊ ጽሑፍ ላይ "ከዲሞክራሲ ጥያቄ ላይ የተጀመረው ክርክር ሳይቦካ ወይ ሌላ አንዳንገገር ብሎም አንድ ገና ዘገባ ሳይታወቅ የአብዮት መድረክ በድንገት እንዳይቀለፍ" ብሎ ያስነዘረው ስጋት ሳምንት ሳይሞላው ደረሰ ማለት ነው ። የአብዮታዊያንን አቋም የሚያንጸባርቁ ጽሑፎች እንዳይወጡ ተከለከሉ:: የአድርባዮቹ "ጽሑፎች" ከሳምንት ሳምንት የአብዮት መድረክን አጣበቡት:: የአብዮታዊያን ጽሑፍ በመቅረቱ ግራ የተጋባው ሕዝብ "እንዳንዶቹ በይቀጥላል ሲቋረጡ ዲሞክራሲ የመንግሥት አንድ ገጽታ በሰሆነ በደርግ ጊዜ አይገኝም የሚለው ጽሁፍ ለምን ከሳምንት ሳምንት ይቀጥላል" ብሎ

መጠየቅ ጀመረ:: ይህንን የሕዝብ ቅሬታ የአዲስ ዘመን አዘጋጅ በጋዜጣው ላይ አተመው:: በሰስተኛው ቀን አዘጋጀው ከሰራው ተነሳ:: የተከፈተውና አድርባዮች እየተለፈለፉ የተጋለጡበት "ክርክር" በዚህ አከተመ::

ታዲያስ ደርግና አድርባዮች "ከክርክር ተረቱና ዲሞክራሲ ዲታወጅ" አሉ ? አላሉም:: የአብዮታዊያንንና የሰፊውን ሕዝብ አፍ በተራ ማጥበርበር ለመቋቋም የጀመሩትን "የትግል ስልት" አፋፉሙ:: በዚሁ ፀረ ሕዝብ የክህደት ጉዳና ከገፉ በአብዮታዊያንና በሰፊው ሕዝብ ላይ ፀረ ሕዝብ አመጽ እንደሚያስፋፉ ጥርጥር የለውም:: ምክንያቱም ሰፊው ሕዝብ ለዲሞክራሲ የሚያደርገውን ትግል ማርክስና ሌኒን እየተውለጋገጡ ሲጠቀሱት እንደሚታየው ሁሉ ቢሮክራሲን ሲያወድም ነፃነትንና እኩልነትን ሲያረጋግጥ አያቆምምና ! የምናየውም ሃቅ ይኸው ነው:: ሰፊው ሕዝብ አሁንም በሰልፍ፣ በውሳኔ፣ በየሰሚናሮቹ ሁሉ ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲለቀቁ እየጠየቀ ነው:: በዚህ አንፃር የሚይዘውና የሚጨበጠው ያጣው ደርግና አድርባዮቹ ሰፊውን ሕዝብ ራሱን በውሳኔ ያሳለፈውን "የለም አላሳለፍህም" በውሳኔ ያላሳለፈውን ደግሞ "የለም አሳልፈሃል" እያሉ በሬዲዮና በጋዜጣ ይቱር ቱለት ጀምረዋል::

የመጀመሪያው ቀሊት የሰፊው ሕዝብ ወኪሎች በቀን ነገር ተሰብስበው ባሳለፋቸው ውሳኔዎች ላይ ደርግና አድርባዮቹ የሚያሰፉት አሳፋሪ መሰራረቅ ነው:: ምሳሌ ? በቅርቡ በዚህ በዲሞክራሲ ጥያቄ ላይ የመላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበርና የሸዋ ክፍለ ሃገር ገበሬዎችማህበራት ተወካዮች፣ የአዲስ አበባ አጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር የጋራ ጉባዔ ያሳለፈውን ውሳኔ መጥቀስ ይቻላል:: የውሳኔው የመጀመሪያ ነጥብ የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ እንዲለቀቁ የሚጠይቅ ነው::

> "በሰፊው ጭቁን ሕዝብ ትግል የተገኙትን ድሎችን ለማስከበርና ለመጠበቅ እንዲሁም በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መሠረት ሰፊውን ሕዝብ በይበልጥ ለማንቃትና ለማደራጀትና ለማስታጠቅ... የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ እንዲለቀቁ"

ምንም እንኳን በዲሞክራሲ ጉዳይ በተነሳው ክርክር ውስጥ ፀረ ዲሞክራሲ አቋም ይዞ በግንባር ቀደምነት የታገለው የአዲሱ ሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ተወካይና እፍኝ የማይሞሉ አራጋቢዎቹ ይሄ ውሳኔ እንዳያልፍ ቢፍጨረጨሩም የነበረት ሃቁ ወዝአደሮች፣ አርሶአደሮች፣ መለዮለባሾችና ሌሎች አብዮታዊያን አድርባዮችን እስከነ ለፍላፊ ክርክሮቻቸው እንዳይሸጡ እንዳይለወጡ አድርገው አጋለጧቸው:: አብዮታዊያን የሙሉትም አቋም በማያዳግም ሁኔታ በአሸናፊነት ወጣ:: ከላይ የጠቀስነው ውሳኔ በ93 ድምጽ ደጋፊ፣ በዜሮ ድምጽ ተቃዋሚ፣ በ13 ድምጽ ያለበጠ አለፈ::



ታዲያስ ደርግና አድርባዮች ምን ዋጣቸው ? ለሰፊው ሕዝብና ለወኪሎቹ ወደር የሌለው ንቀት በማሳየት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ /ጥቅምት 22 ቀን 1970 ዓ.ም/ እንደሚከተለው አድርገው ቀየሩት:-

> "በሰፊው ጭቁን ሕዝብ ትግል የተገኙትን ድሎች ለማስከበርና ለመጠበቅ እንዲሁም በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መሠረት ሰፊውን ሕዝብ በይበልጥ ለማንቃት፣ ለማደራጀትና ለማስታጠቅ... ዲሞክራሲያዊ መብቶች አስፈላጊ መሆናቸውን ተነጋገሩበታል"

እንዲህ አርገው "ውሳኔ" የለም ! "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ እንዲለቀቁ" መጠየቅና እንዲሁ "ስለዲሞክራሲያዊ መብቶች አስፈላጊነት መነጋገር" የአብዮታዊ ትግልንና የፀረ አብዮት መሠሪነትን ያህሉ ልዩነት እንዳለው ገላጽ ነው:: ግን የደርግና የአድርባዮች ቀሊት በዚህ አያቆምም:: የደርግ ቀጥር ታጋዮች ባሁኑ ወቅት "ፈርጣጭ"፣ "ከሃዲ"፣ "ሰርጎገብ" እያሉ አብዮታዊያንን ለአድሃሪው ቢሮክራሲ መጠቆምና ማሣሠር፣ በደቡብ ደግሞ በትምክህተኞች ማስረሸን ሥራዬ ብለው እንደያዙ ማንም የሚያውቀው ጉዳይ ነው:: በአዲስ አበባ ከተማ እንኳን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ በወጣቶችና በታጋይ ሴቶች ላይ የተለየ ክትትል እየተደረገ ብዙ ታጋዮች በእስር ላይ እንደሚገኙ የታወቀ ነው:: የሰፊው ሕዝብ ተወካዮች ይህንን ጥቃትና የታጋዮችን መታሰርና መንገላታት በመቃወም በውሳኔያቸው ነጥብ 4 ላይ የሚከተለውን አስፍረዋል:-

> "በአድሃሪያን ጥቃት የታሰሩ ተራማጅ ኃይሎች በሕዝባዊ ድርጅቶች ማለትም በመኢሠማ፣ በገበሬ ማህበራት፣ በከተማ ነዋሪዎች ማህበራትና በሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ተወጣጥቶ በተቋቋመ ኮሚቴ ጉዳያቸው እየተመረመረ ባስቸኳይ ውሳኔ እንዲሰጥበት ወይፈትም በሚታሰሩም ሆነ በሚፈቱ ፀረ አብዮተኞች ላይ ይኸው ኮሚቴ እንዲሳተፍበት" የሚል ነበር::

ደርግና አድርባዮቹ በቀሊትና በሕዝብ ንቀት ጉዳና ላይ ወደፊት በመራመድ ይሄንን ውሳኔ በጋዜጣና በሬዲዮ እንዳይገለጽ አደረጉት;: የመላ ኢትዮጵያ ወዝአደር ተወካዮች፣ የሸዋ ክፍለ አገር አርሶአደሮች ተወካዮች፣ የመላ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ባጥሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ጭቁኖች ተወካዮች በቀን ነገር አራት ቀን ሙሉ ተወያይተው በ24 ነጥብ ያሳለፉት ውሳኔ እፍኝ ከማይሞሉ ፀረ ሕዝቦች አቋም ጋር እንዲመሳሰል ተቦሎ ተከርክሞ ተደለዘ ባለ 23 ነጥብ ውሳኔ ሆኖ ለሕዝብ ተገለጸ:: ከሰረትና ክህደት ይሏል ይህ ነው !

ሌላም ብዙ ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል:: ሌ/ኮ አጥናፉ አባተ ላይ እርምጃ ሲወሰድ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች አጠቃላይ ማህበር ባወጣው

መገለጫ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለገደብ እንዲለቀቁ ጠይቆ አስተላለፈ:: ደርግና አድርባዮቹ ለነሱ የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ብቻ በሬዲዮና በጋዜጣ ለፍፈው የማህበረን አብዮታዊ ጥያቄ ግን እንዳልነበረ አፍነው አስቀሩት::

በዚህ ሁኔታ ዲሞክራሲ እንዲከበር፣ ታጋይ ወዛደሮች፣ አርሶአደሮች፣ መለዮለባሾች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ የጭቁን ብሄረሰቦች ታጋዮችና ሌሎች አብዮታዊያን እንዲፈቱ ከያለበት የሚቀርቡትን ጥያቄ ከሕዝቡ ለመሸሸግ በመከረ ምን ያስደንቃል? በሰላሌ፣ በደብረብርሃን፣ በሃይቆችና ቡታጅራ፣ በሃዲያና ከንባታ፣ በአርባጉጉ... ወዘተ የታሰሩት ጓዶች እንዲፈቱ፣ አድርባይ የሕዝብ ድርጅቶች አባላት እንዲወገዱ እየጠየቁ የተደረጉትን ከፍተኛ ሰላማዊ ሰልፎች እንደሌሉና እንዳልነበረ አድርገው ቢያፍኗቸው ምን ያስገርማል?

ከደርግና ከአድርባዮቹ ከዚህም የባሰ ቅሌት ተፈጽሟል:: የተባለውን መስረቅ ብቻ ሳይሆን ያልተባለ መጨመርም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወዛደሮች እየታዘቡ የሄዱት ነገር ሆኗል:: ደርግና አድርባዮቹ የፈጠራ ውሳኔዎችን በሬዲዮ ማስተላለፍ ይዘዋል!!! ባለፈው ሰሞን በአንድ አካባቢ የሚገኙትን ወዛደሮች የሚወክሉ ተጠሪዎች ተሰብስበው "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች አሁኑኑ" የሚለው መፈክር ተወግዟል በለው በሬድዮና በጋዜጣ ያስተላለፉት ውሳኔ እንኳን ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ ለራሱ ለአንድ ወዛደር እንግዳ ነገር ሆኖበት አድርባዮችን የባሰውን መሳቂያ ያስደረጋቸውና የባሰውን ያጋለጣቸው ቅሌታዊ ድርጊት ሆኗል:: ግን ተጠረውን በለው አይቀውትም:: በመደብ ትግል ይሉንታ የለምና ገና ብዙ የፈጠራ ውሳኔዎች የነአዲስ ዘመንን አምደኞች እንደሚሞሉት ካሁኑ መተንበይ ይቻላል::

የደርግን ታሪካዊ ሚና ለተረዱ ለሰፊው ሕዝብ ያለመታከት ለሚያስረዱ ለንቁ አብዮታዊያን ይህ ሁኔታ ፈጽሞ የሚገርም አይደለም:: ደርግ፣ አድሃሪው ቢሮክራሲና የቀኝ አድርባዮች ክርክር ሲያሰቀባቸው ወደ ተራ ማጭበርበር፣ ያለሳካ ሲል ደግሞ ወደ ፀረ ሕዝብ አመጽ እንደሚሸጋገሩና በዚህም የኢትዮጵያን አብዮት ሂደት ለመግታት እንደሚፍጨረጨሩ ሳይታለም የተፈታ ነገር ነው:: አብዮታዊያን በዚህ አይደናገጡም::

የሆነ ሆኖ ደርግና አድርባዮቹ በንደዚህ አይነቱ ድርጊታቸው በክህደት ጎዳና ላይ ምን ያህል "እንደገፉ" ማረጋገጥ ይቻላል:: በተጨማሪም እንዲህ አይነቱ ድርጊት ደርግና አድርባዮቹ ከነሱ ቁጥጥር ውጭ እንዳይነሱና እንዳይደራጁ ያፈኑትን ሰፊው ሕዝብና ተወካዮቹን ምን ያህል እንደሚንቁ በግልጽ ማሳየታቸው እንደሆነ ግልጽ ነው:: በዚሁ አንፃር ግን የወላዋዮቹን፣ ያድርባዮቹን ክህደት ሊቋቋም በሚችል ታታሪነትና ቆራጥት ማህበራችን ከሌሎች በፕሮግራሙ ከፀኑ አብዮታዊያን ጎን ይሰለፋል:: የሰፊውን ሕዝብ ተወካዮች ውሳኔን በማክበር አሁንም



ለፕሮግራሙና ለሰፊው ሕዝብ ጥያቄዎች መታገሉን ይቀጥላል:: የሰፊው ሕዝብ ተወካዮች ውሳኔ ደርግ በርዘ ደለዘ እንዳቀረበው ሳይሆን በሃቁ ይዘቱ ተገንዝበው አባላቶቻችን እንዲታገሉለት በማሰብ እነሆ የውሳኔውን ሙሉ ይዘት እንደሚከተለው ያቀርባል::

በዚህ ከሕዝባዊ ድርጅቶች ተወካዮች ውሳኔ ጋር ከአዲስ አበባና ከአካባቢው ከሚገኙ የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶች የተወጣጡ የወዛደር ተጠሪዎች ባለፈው ሰሞን የበተኑትና እንደሚጠበቀው ሁሉ ደርግና አድርባዮቹ ለማፈን የሞከሩት መግለጫና ውሳኔ ለአንባቢያችን እያቀረብን ይህን የወዛደሮች ድምጽ ደርግ በሬዲዮና በጋዜጣ ከሚያስተጋባቸው የፈጠራ ውሳኔዎች ጋር እያነጻጸሩ እንዲያነቡ እንጠይቃለን::

ከብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ጋር ወደፊት!
ከፕሮግራሙ የተንሸራተቱት አስመሳዮች በሰፊው ሕዝብ ክንድ ይደቃሉ!
ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ ባስቸኳይ!
በሃቀኛ አብዮታዊያን ላይ የሚካሄደው ፀረ ሕዝብ ዘመቻ ይቁም!
የታሰሩት ሃቀኛ አብዮታዊያን ይፈቱ!
የብሄር ትምክህተኞች በጭቁኖች የተባበረ ክንድ ይወድማሉ!
የነፃ፣ የተደራጀና የታጠቀ የሕዝብ አመጽ ያሸንፋል!

—//—

የመላው ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር

የሸዋ ክፍለ ሀገር ገበሬዎች ማኅበር

የአዲስ አበባ አጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች ማኅበር

በመላው ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ጽ/ቤት ከጥቅምት 14 ቀን 70ዓ.ም. እስከ ጥቅምት 17 ቀን 70ዓ.ም. ድረስ ባደረገው ስብሰባ በጊዜው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተነጋግሮ የሰጠው መግለጫና ውሳኔ፤

በየካቲት 66 የፈነዳው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝቦች ግብታዊ አብዮት በየጊዜው የገጠሙትን የፀረ—አብዮት ወጥመዶች እንደጊዜውና እንደሁኔታው በረቀቀ መንገዱ እያለፈና ድሉን በድሉ ላይ እየተጎናጸፈ መሄዱ የማይካድ ሀቅ ነው።

ትግሉ የመደብ ትግል እንደመሆኑ፤ በገዥና በተገዥ በበዝባዥና በተበዝባዥ መሀከል ያለው ሳራኔ ክር ከመበጠሱም በላይ የመደብ አሰላለፉም እየጠራና መንገዱ እየያዘ ይገኛል።

ይኸንን የመደብ አሰላለፍ የፈጠረው በአብዮታችን ሂደት ሰፊ ሕዝቦች የተጎናጸፉት ድል ነው።

አብዮታችን ሕዝባዊና ሥር ነቀል በመሆኑም፤

1ኛ/ ለዘመናት ተንሰራፍቶ የኖረው ዘውድ መገርሰሱ፤

2ኛ/ መሬት ለታሪካዊው ባለቤት ለአርሶ አደሩ እንዲሆን መደረጉ፤

3ኛ/ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መዋሉ፤

4ኛ/ የማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅቶች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መዋላቸው፤

5ኛ/ የትግላችን መርሀ የሆነው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መታወጁና ሌሎችንም የመሳሰሉትን ድሎችን ተጎናጽፈናል፤

በሰፊው ሰፊ ሕዝብ እነዚህን የማይናቁ ድሎች ለመጎናጸፍ ትግል በሚያደርግበት ጊዜ አድሀሪው ወገን እጁን አጣጥፎ አልተቀመጠም።

የሰፊው ሰፊ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀንደኛ የውስጥ ጠላቶች የሆኑት ኢ.ሕ.አ.ፓ. ኢ.ዲ.ዩና. የኤርትራ ተገንጣይ ቡድኖች በበላይ ጠባቂያቸው ኢምፔሪያሊዝም በአረብ አድሀሪ የገዥ መደቦች አብ ተባባሪነት አብዮቱን ለማኮላሸት ከፍተኛ መፍጨርጨር አሳይተዋል እያሳዩም ናቸው።

በሰፊው ሕዝብ ለንቃት፤ ለድርጅትና ለትጥቅ በሚታገሉበት ወቅት፤ ፀረ—ንቃት፤ ፀረ—ድርጅትና ፀረ—ትጥቅ አቋም በመውሰድ በሰፊውን ሕዝብ ለማወናበድ መሞከራቸው ለማንም ግልጽ ነው።

ከዚህም ሌላ የመሬት ለአራሹን በመቃወም፤ ለዘመናት በባርነት ኖሮ ዛሬ ግን ነፃ ከሆነው ሰፊው ገበሬ ጋር ያላቸውን ጠላትነት በገሀድ አስመስክረዋል።

የወዛደሩ ርዕዮተ ዓለም መንገዱ ሕዝባዊና ብቸኛ በመሆኑ [illegible] ረው የሰፊው ሕዝብ ጠላት መሆናቸው በገሀድ ቢታወቅ እንዲሁም በተለይም ኢ.ሕ.አ.ፓ. ወደ ተራ ነፍሰ ገዳይ ተሸጋግሯል።

/2/...

ETHIOPIAN TRADE UNION



ኢ.ሕ.አ.ፓ. ግልጽ ፈጥሮ የመግደል ትግሉን አፋፍሞአል። ሆኖም በየጎዳናው ዝም ብሎ አብዮታዊ ተራማጆችን መግደሉና ሽብር ፈጥሮ አብዮቱን ለመቀልበስ መሞከር በሀገራችን አብዮት ብቻ የታየ ባይሆን በማንኛውም አብዮት ባካሄዱ ሀገሮች የደረሰ ለመሆኑ ታሪክ ያስተምረናል።

አብዮቱ በሕዝባዊ መንገዱ እየቀጠለ አድሀሪያንን እየደመሰሰ ቢሄድ እንዲ ወሳኝና መራራ ወቅት መድረሱ አልቀረም።

ይህም መራራና ወሳኝ ወቅት በሰፊው ሕዝብ ታግሎ የመጨረሻውን ድል የሚጎናጸፍበት ቢሆን አድሀሪያንም ለመጨረሻ ጊዜ የሚንፈራገጡበት ወቅት ነው።

ዛሬ በሀገራችን የሚካሄደው አብዮት የደረሰበት ወሳኝ ወቅትም ይኸው ነው። በአብዮታችንና በሀገራችን ከውጭ በአድሀሪ የሶማሊያ የገዥ መደቦችና የዓረብ አድሀሪ ገዥ መደቦች በኢምፔሪያሊዝም የበላይ አቀነባባሪነት አድሀሪና ግልጽ ወረራ እየተካሄደብን ነው።

ከውስጥም ደግሞ ከወራሪው ጠላት ጋር አብሮና ጎን ለጎን የሆነ የአብዮት ተቃዋሚ ሁሉ አድሀሪውን ቢሮክራሲ ተገን በማድረግ በኢ.ሕ.አ.ፓ.፤ በኢ/ዲ.ዩና በኤርትራ ተገንጣይ ቡድኖች እየተቀነባበረ ነው።

አብዮቱ የወለዳቸውን ሕዝባዊ ድርጅቶች ለማፍረስ በከተማም ሆነ በገጠር የሚገኙ ድርጅቶችን ሮሾና ሰርጎ ቢገባም አድሀሪያንም ተራማጅ በመምሰል ሁኔታ ተራማጆችን እየመቱ ማሰር ጀምረዋል።

በተለይም በአዲስ አበባ ከተማችን ሕዝባዊ ድርጅቶች በተቀነባበረ ኃይል አድሀሪያንን ሲደመስሱ በሚሯሯጡበት ጊዜ መሪ ተዋናዮቹ የዱሮው ቢሮክራሲ መብት ሰጭዎች ያለ ገደብ ባለመሰየቱ የአድሀሪው ቢሮክራሲ ተፅዕኖ ሊያጋጥማቸው አልቻለም።

1/ አድሀሪው ቢሮክራሲ ዛሬ በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝቦች ትግል ላይ ጫና ለማሳደር በሚያደርገው አሻጥር፤

በአሁኑ ጊዜ በየአርሺ ድርጅትና በፋብሪካዎች፤ በጥቃቅን የማምረቻ ድርጅቶች ውስጥ የመንግሥት ሰርጎ እንዲያደርጉ በወቅቱ እንዲደበስበሱ በወቅቱ እንዲደራ ረቡ ከማእከላዊ በላይ ለአሁኑም የተቃረ ተራው ሰፊ ወዛ አደር በጥቅት ላይ አሻጥር ሲሰራበት ዝም ብሎ እያየ በሐቀኝነት ተቃውሞ ቢያሰማ ይሕ ይገባኛል የማይል ጠቢብ ሰው ነኝ በማለት ክፍና ከመያዙም ሌላ በሀሰት ወንጀል እንዲታሰር ያደርጋል።

በጥቃቅን የማምረቻ መሣሪያዎችና ድርጅቶች ያሉ ባለንብረቶች ወዛ አደሩን ለመበተንና ማምረቻውን ለማዳከም ሥራው እንዳይንቀሳቀስ ዕቃ በማሸሽና በመሸጥ ያለውን የገንዘብ ክምችት በማሸሽና ከዚያት በግዳጅ ሌላ ሥራ ላይ በማዋል የሀብት የሂሣብ መዝገብ በማዘጋጀት በአብዮቱ ላይ ቢያሤሩ የነቁ ወዛ አደሮችም ነበረበት ጊዜ ከስራቸው ከረሰንቸው በሃሰት ገንዘብ ከሥራ ገበታቸው እንዲ...

/3/...

ETHIOPIAN TRADE UNION

አያሉ የተነሱ ዐማፂያንን ለየዘረጉ ሀሞኛችን ወ. አደሮች አናርከስተ ነው አያ ሰኝ በሀሰተ ከአድሀሪው ቢሮክራሲ ጋር በማበር ያባሰራሉ::

በ<u>ፖለቲካ</u>: አብዮታዊ ፍሬ አስኪያጆችና ባለንብረቶች አንደ አብዮተኛ ለመቅጠር በዘመቻ ጨ የመናወ ባቢያ ትዋት ከማገኘታቸውም በላይ አነሱ ታጋዮች ጥቁኑ ወዝ አደር. ገን ፀረ— አብዮተኛ ሆኖ በየቢታው ወ. አደሩን ሲፈሩን በማባበርና ከሥራ በማስወጣት አፈናም በመያ ማተበረ ላይ ከፍተኛ ተዕዕኖ በማድረግ አብዮታችንን በአፈርስነትና በገንዘብ ለመቅ.ብስ በመሰጣር ላይ ናቸው::

ገ/ የቡግ ወራሪ ዛሬ የኢትዮጵያን ሰራ ጉልበ በጉዛና በሃይማኖት አሰያይቶ ለማጋ ት በመጣር ላይ ቢሆን ከውስጥ የሚገኙ አድሃሪያች ደግሞ ለመሬው ጋራሪ መሣሪያ ሁኔታንና አጋጣሚ ለመፍጠር የዲሞክራሲ መብትና የብሔረሰብ እኩልነት እንዲታ ፈንና የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በትደረጃው በሥራ እንዳይተረጉ ም ከየተኛውም ጊዜ በበለጠ እየተሯሯጡ ናቸው::

በ<u>ሀቢሎ</u>፤ ሕዝባዊ ድርጅቶች እንዲፈርሱ፤ የአብዮት ጥበቃ ጓዶች በአብዮታዊ ሥራ ቸው ላይ አንዳይሰማሩ ጸረዕዝ በመፍጠር ማበረታቻ በመበተና. የሚገባቸው ን ዕውቀት በመንፈግ ሕገባዊ ድርጅቶች አንዲደክሙ በማድረግ ላይ ናቸው::

<u>በራሱ የኢትዮጵያ ሠራተኛ ሕዝብ ሆይ!</u>

በመራራ ትግልህ ያገኘሀቸውን ድሎች ከአፍህ ለመንጠቅና አብዮትህን የፊውዳ ወደ ስጡ በላው አስከፊ ሥርዓት ለመመለስ የሚደረገው ኑዝጊት ከመቼውም ይበልጥ አ የተፋፋመ መሆኑን ልትገነዘብ ይገባል::

ከአንተ ከአብዮቱ ባለቤት በበተቃር ለአናት ጠገርህና ለአብዮትህ ሲጠነቀቁ የሚገደዱ አንዱም አካል የለም፤ ታሪክ በራሱ አንተው ነህና::

ስለዚህ በየአትዋርጡ የመደብ ትግልን ለያፋፋምክ የተሰነዘረብህን ጥቃት ለመመከትና አብዮትህንና አንድነትህን ለመጠበቅ በንሉሱ በአብዮታዊ ወጥ ንቁም ህ ተነሣ!!!



1. በሰፊው ጭቁን ሕዝብ ትግል የተገኙትን ድሎች ለማስከበርና ለመጠበቅ እንዲሁም በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መሠረት ሰፊውን ሕዝብ በይበልጥ ለማን ቃትና ለማደራጀትና ለማስታጠቅ ብሎም በትግሉ ተቀጭን የሚያስጠብቅለትን የወዝ አደር ፓርቲ መስርቶ ለሥልጣን ለማብቃት፣ ሰፊውን ሕዝብ በጉዛና በሃይማኖት ለ መከፋፈል በየጊዜው የሚነሳሰውን የአድሀሪያን ሴራ ለማክሸፍና ብሔረሰቦች በመ ካከላቸው ያሉትን መሰረተኛ ቅራኔዎች አስወግደው በእኩልነትና በአንድነት እዲሲ ትን ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት የሚያደርጉትን ትግል በይበልጥ ለማፋ ፋምና ለማገዝ፣ ተራማጅ ሐይሎች ከሠፊው ህዝብ ጋር በመዋሃድ እንዲያነቁትና አ ንድያደራጁት ለማገዝና በመካከላቸው ሊኖሩ የሚችሉትን መሰረተኛ ቅራኔዎች አስወ ገደው ውህደት እንዲፈጥሩ ለማገዝ፣ የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ እን ዲሰጥ ::

2. በአዲስ አበባ በጊዜው ሰፍኖ የሚገኘውን ነጭ ሽብር ወደ ቀይ ሽብር ለመለወጥና የአብዮት መዲና ለማድረግ ከቢሮክራሲው ቁጥጥር ነፃ በሆነ መንገድ ከወዝ አደሩ ከገበሬውና ከከተማ ነዋሪዎች ከጭቁኑ መለዮ ለባሽ በተውጣጡ የአብዮት ጥበቃ ጓ ዶች አስቸኳይ የተሟላ አሰሳና ምንጠራ እንዲደረግ ::

3. ከገጠር ሸሽተው ከተማ የገቡና የመሸጉ የፀረአብዮት ሴራ የሚጠነስሱና በአብዮቱ ወገኖች ላይ ግድያ የሚያስፈጽሙ የሚያቀነባብሩ የመሬት ከበርቴዎችና አድሐሪ ቡ ድኖች፤ ፀረአብዮተኞች በአስቸም የሚገኙ ጥምር በገበሬ ማህበራት ቁጥጥር ወደም ርት ስራ እንዲሰማሩ ::

4. በአድሐርያን ጥቃት የታሰሩ ተራማጅ ጓዶች በሕዝባዊ ድርጅቶች ማለት ከመ.ኢ.ሠ. ማ.፤ ከገበሬ ማህበራት፤ ከከተማ ነዋሪዎች ማህበራትና ከሕዝብ ድርጅት ጊዜያዊ ጽ/ቤት ተውጣጥቶ በተቋቋመ ኮሚቴ ጉዳያቸው እየተመረመረ ባስቸኳይ ውሣኔ እንዲ ሰጥበት ወደፊትም በሚታሰሩም ሆነ በሚፈቱ ፀረ አብዮተኞች ላይ ይኸው ኮሚቴ አ ንዲሳተፍበት ::

5. የወዝ አደሩና የአርሶ አደሩ የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት የምርት ግንኙነቶች ከ አድሐሪው ቢሮክራሲና ከሻጥረኛ ነጋዴዎች ተጽዕኖ ወጥ የሚሆንበት መንገድ እንዲ ዘጋጅ፤ የምርት ዋጋ ተመና በሚዘጋጅበት ጊዜ የሰስተ ሕዝባዊ ድርጅቶች ተጠሪዎ ች ተካተው እንዲኖር እንዲደረግ ::

6. የሰፊው ሕዝብ መታጠቅ የአብዮቱ ዋስትና እንደመሆኑ መጠን የተጠቀ ፕሬትና ይዞ ት ፀረ አብዮት ኃይሎች ከታጠቀት ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን፤ እንዲሁም ያልታጠቁ ማህበራት አስቸኳይ አሰሳና ምንጠራ ከተደረገ በኋላ እንዲታጠቁ እንዲደረግልን፤ ሰውር ትጥቅ እንዲፈታ ::

7. ብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻው ገቡን እንዲመታና አብዮታዊ አመራሩ በተገናኘው አድሐ ሪ ቢሮክራቶች ሠርገው እንዳይገቡ ትንታቄ እንዲደረግ፤ በሃገራዊ-ዘመቻው ዱላ አ ንዳይመታ በዘመቻው ውስጥ መሰናከል የሚፈጥሩ ተራማጅ የሆኑ አድሐሪ የቢሮክራ ቢሮክራቶች እንዲመነጠሩ ::

8. በከተማችን የሚገኙ የፀረ አብዮት አስር ቤቶች የፀረ አብዮት ሃይሎች መሸሸጊያና ማሰልጠኛ መሆናቸው ቀርቶ በገበሬ ማህበራት ቁጥጥር ስር ሆነው በእርሻ ቦታ የ

ሚገኙት ፀረ አብዮተኞች የግዲያ ሥራ እየሠሩ በምርት ሥራ ላይ እንዲውሉና እንዲታረሙ እንዲደረግ እንጠይቃለን ። የፀረ አብዮት ኃይሎች እስር ቤቶች ከከተማችን ይነሱልን ።

9. ለዘማቾችና ለቤተሰቦቻቸው ልዩ እንክብካቤ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ በጦር ግንባር ያሉትን ዘማቾች በቦታ የሚያስማሩ የሚያጠናክሩ ሕዝባዊ ድርጅቶች የተውጣጣ ኮሚቴ እንዲቋቋም እንጠይቃለን ።

10. የገበሬ፣ የወዛአደሩ፣ የከተማ ነዋሪዎች ማህበራትና የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ስለኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ለመወያየትና የትግል ስልት ለመነጋገር እንዲችሉ በ3 ወር አንድ ቋሚ ስብሰባ ይደረጋል ።

11. የከበርቴ ልጆች ማታ ገንዘብ እየከፈሉ እየተማሩ ቀን ያለስራ የጭቁን ልጆች እንዳይማሩ በፀረ ሕዝብ ዑርጌት የተከማሩ ስለሆነ የማታው ትምህርት ስራ ላላቸውና እድሜያቸው ከትምህርት አለም ላለፈባቸው ብቻ እንዲደረግ ። በተጨማሪም በማዕማሩና እንቶዉማሩ በማገፋፋ መምህራን ላይ የማያዳግም እርምጃ እንዲወሰድ

12. በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መሠረት የሴቶች ማህበራት እንዲሁም የወጣቶች ማኅበራት ከቀበሌ ጀምሮ እስከ አጠቃላይ ማህበራት ድረስ ለመቋቋም እንዲችሉ ሕዝባዊ ድርጅቶችና የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ማህበሩን በማቋቋም በኩል ትግላቸውን እንዲያፋፍሙ ።

13. ስራ አጦች ለፀረ አብዮት ዑርጌት ተባባሪ ስለሚሆኑ በከተማችን የሚገኙ ሥራ አጦች የወዛ አደሩ፣ የአርሶ አደሩ፣ የከተማ ነዋሪዎች ማህበራትና ጉዳዩ የሚመለከተው የመንግስት ተጠሪዎች የሚገኙበት ኮሚቴ ተቋቁሞ የሠፈራ ፕሮግራም በአስቸኳይ እንዲዘጋጁ ።

14. በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መሠረት የብሄረሰብ እኩልነት ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እየታየ በስራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ ።

15. የገበሬ ማህበራት በትግላቸው ያስፈቱትን መሣሪያ በአዲጠሪያን ሰሩና ጥቀማ እንዲፈቀድ እንዲደረግ ።

16. ከገበሬ ማኅበርም ሰው ተወክሉ ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሸቀጣሸቀጥ ለመገዛት በሚመጡበት ጊዜ የሚሰጠው የእቃ ዝርዝርና የዋጋ ተመን በዛት ሻው ድርጅት ባጸደቀ ለተወከለበት የገበሬ ማህበር እንዲያሳውቅ ።

17. አብዮታዊት ኢትዮጵያ ብሄራዊ አብዮታዊና ህዝባዊ ጦርነት በማካሄድ ላይ ባለችበት በአሁኑ ወቅት አሻጥረኛ የግል አሠሪዎች ወዛደሩ እንዲሰቃይና በአብዮቱ ላይ እንዲያምጽ ለማድረግ ገበያ አጥቻለሁ ከሥሬአለሁ በማለት የተጭበረበረ መዝገብ እያቀረቡ ድርጅታቸውን በመዝጋት ከፍተኛ የኢኮኖሚና የሶሻል አሻጥር እያካሄዱ ናቸው ።

የውጭ ሀገር አሠሪዎችም የድርጅታቸውን ንብረት እየጠጡ [illegible] ጉር እየዘጉ ስለሆነ የሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር [illegible] ክትትል ቆሥራውንና የሒሳብ ይዞታቸውን ከተከከለኛው መዝገብ [illegible] እንዲቋምና በዚህም ሥራ የድርጅት ማህበራት የኢንዱስትሪ [illegible] መ.ኢ.ሠ.ማ. እንዲሳተፉበት እንዲደረግ ።



18. በማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅቶች ውስጥ ያሉ አድሀሪ አሠሪዎች ኢኮኖሚያችንን እንኮታኩተው በዚያም ባቢያ አብዮታችንን ለመቀልበስ የሚመቻች ስለሆነ መንግሥት ከወዛደሩ ጋር ሆና ቁጥጥሩን በማጥበቅ በተጨባጭ ማስረጃ ፀረ አብዮተኛነታቸው ሲጋለጥ የማያዳግም እርምጃ እንዲወሰድባቸው እንዲደረግ ።

19. በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ አብዮት ላይ ከውስጥም ሆነ ከውጭ የተነሱበት ሃይሎች የሰፊውን ሕዝብ የበለጠ መስዋእትነትና የመደብ ትግሉን ማፋፋም የሚጠይቅ ሆኗል ይህንን በሥራ ለመተርጎም መ.ኢ.ሠ.ማ.፣ የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት፣ የገበሬ ማህበራት በየበኩላቸው በመሃላቸው ሰፊ የፖለቲካ ቅስቀሳ እንዲያደርጉና በዚሁም ጥረታቸው የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤትና ተራማጆች እንዲተባበሩዋቸው ።

20. የትግላችን አንድ አንፃር ምርትን ማሳደግ ስለሆነ ይህንን ለማድረግ መ.ኢ.ሠ.ማና የገበሬ ማህበራት ሰፊ ቅስቀሳና ዝግጅት እንዲያደርጉ ።

21. ዐረ ሕዝብ፣ ዐረአንድነት፣ ፀረ አብዮት ፕሮፓጋንዳን ቅስቀሳን ለመቋቋምና የሕዝባዊ ድርጅቶችን አቋም ለማጠናከር እንዲሁም ሰፊው ሕዝብ የበለጠ ንቁ ተደራጅቶና ታጥቆ በአንድነት ክንዱን በፀረ አብዮቶች ላይ አንስቶ የቀለበሷውን ሴራ እንዲያከሽፍ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ሰፊውን ሕዝብ ለመቀስቀስና በይበልጥ ለማንቃት ያልተቆጠበ አገልግሎት መስጠት አለባቸው ። ማለትም ለሠራተኞች ማኅበራት፣ ለገበሬ ማኅበራት፣ ለቀበሌ ማኅበራት፣ ለሴቶች ማኅበራትና ለወጣቶች ማኅበራት ሰፊ ያለ ፕሮግራም በመስጠት አሁን የሚሠራበትን ጊዜ የማስታወቂያ ድርጅት ማራዘም እንዳለባቸው እየጠየቅን፣ የፕሮግራሙ ይዘት አብዮታዊ እንዲሆንና የጊዜውን ተጨባጭ ሁኔታ የሚያገናዝብ መሆን እንዳለበት እናስገነዝባለን ።

22. አድሃሪው ቡርዧዚ የኢምፔሪያሊስት ጀሌነቱን በማገበያረቅና ለአብዮቱ ቀለበሳ ሴራ ቀንበሩን በገበር በመግለጽ ላይ ነው ። በተለይም ለአብዮቱ ዕድገትና ለሕዝባዊ አብዮታዊው ጦርነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በሚያደርጉት በአየር፣ በየብስና በባሕር መገናኛዎች በመለዋወጫ እቃዎች፣ በጎማዎች፣ በወዛ አደሩ የምርት እድገቶችና እንዲሁም በአርሻ ሰብል ምርት ውጤቶች ላይ ማተኮሩን በተጨባጭ ሁኔታ ስለተደረሰበት የሠራተኛው ማኅበራት ተጠሪዎች በየድርጅታቸው ውስጥ ሙሉ የአስተዳደር ተሳትፎ እንዲኖራቸውና እንዲሁም ዘመቻውን በሚመለከተው የትራንስፖርት ማስተናበሪያ አቋምና በሌላውም አብዮቱን በሚመለከቱ ድርጅቶች ውስጥ ሙሉ ተሳታፊነትና ቁጥጥር እንዲኖራቸው ።

23. የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ ለብዙ ዘመናት ሲረገጥበትና ሲበዘበዝበት የቆየውን ፊውዶ ቡርዥዋ ሥርዓተ ማህበር እንኮታኩቶ በመጣል በምትኩ የዓለም አቀፍ ጭቁን ሕዝቦችን የበላይነት የሚያረጋግጠውን የሕብረተሰባዊነት ስርዓተማህበር በመተካት በኢትዮጵያ ውስጥ በአፍሪካ ቀንድ ላይ ሣይንሳዊ ጠንካራ አብዮት በማካሄድ ላይ መሆኑን የተረዱትና በጥብቅ የሚከታተሉት ፊውዳሊዝም፣ አለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝምና አቀንቃኞቻቸው ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ይህን [illegible] የጭቁን ሕዝቦች የአርነት ችቦ የሆነውን አብዮት ለማፈን [illegible] አሁኑ ወቅት ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ ወይላቸውን [illegible] ጀሌዎቹያውን በመከፈት ገሃድ ጦርነት በማካሄድ ላይ ስለሆነ [illegible] ሕዝብ የሕብረተሰባዊነትን ሪዮተዓለም የሚከተሉ ሃገሮችና [illegible] እንዲሁም የመላው

ዓለም ጥቅን ወዘ አደርኘ በቁሉ ባይበለጥ ከንት እንዲኹ እስ ቸኰይ የሆነ አብ ዮታዊ ጥሪ ያደርጋል ።

24. በበጨራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ውስጥ በዝርዝር እንደተገለጸው በጨራዊ ከበርቴዎችና የውጭ አገር አሰሪዎች ገንዘባቸውን በሥራ ላይ በማዋል አራሳቸው ተጠቃሚ የአገሪቷን ኢኮኖሚ ለመገንባትና ለማሳደግ ለሚደረገው ትግል የከበርቴዎች ድርሻ በሚገባ ከመጠቀም በላይ አብዮትን እስከሚታረቅ ድረስ ከሕዝባዊ አመጽ ጋር መጋዝ እንደሚችሉ ተገልጿል ። ይህንኑ አባባል እውን ለማድረግ አብዮታችንና ብሄራዊ ነፃነታችን አሁን ወሰኝ ደረጃ ላይ በሚገኝበት በአሁኑ ወቅት ከፍተኛና መለስተኛ ከበርቴዎች የፀረ ካፒቴውን ብሔራዊ ጦርነት በመደገፍና በአፋጋሪው የቦማሌ መንግሥት የተቃጣብንን ወረራ በመቃወም ለዘማቾች ሠራዊት ሥንቅ በመርዳት ረገድ አስተዋጽኦ ቢያደርጉም በዚህ አርዓያ ባቢያ በሕግ የፈረሰውን የቀድሞ የአሰሪዎች ፌዴሬሽን ለመመስረት ከመቃረባቸውም ሌላ በአሰሪዎች ስም በዓለም ሠራተኞች ማኅበር ላይ እስከ ዛሬ በመከፈል ላይ ሲገኙ በአገር ውስጥም በአሰሪዎች የሚደገፍ የመበዝበዝ ድርጅት በመፍጠር ጥቅን ሠራተኛ ተመዘዛኝ አንጻን ባይሆን ተቃራራቢ የሆነ የጉለበትን ዋጋ እንዳያገኝ ሕጎችን በማጣመም በአሠሪና በሠራተኛ መካከል የሚደረጉ የጋራ ስምምነቶች በአጭር ጊዜ ሊያልቁ የሚችሉትን ከዓመት በላይ እንዲጓተቱ ያደርጋሉ::

ስለዚህ በሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ 64/68 የፈረሰው የአሰሪዎች ፌዴሬሽን ሕልውና እንዲለው ተቃጥሮ በዓለም ሠራተኞች ማኅበር መደበኛ ስብሰባ ላይ መካፈሉንና በአገር ውስጥ የሚያደርገውን ማኀበራራት ጉባዔው በጽኑ ይቃወማል ።

ሰፊው ሕዝብ ያሸንፋል

ALL ETHIOPIA TRADE UNION



ከ ታጋይ ወዝአደሮች
ለ መላው ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር /መኢሠማ/

---

የኢትዮጵያን አብዮት ዛሬ የደረሰበትን ደረጃ አይነተኛ የሚያደርጉት ባህርያት ምንድን ናቸው ? አብዮታችን ዛሬ ምን ደረጃ ላይ ደርሷል ? ከገንዛህበ አብዮቱ ገፍቶ ድል እንዲመታ ሰፊው ሕዝብ በተለይ ተራማጆች ምን እርምጃ መውሰድ አለባቸው ?

አብዮቱ ገሩን እንዲመታ፣ ሰፊው ሕዝብ ጠላቶቹን ደምስሶ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያ እራዉትፈጠር የሚሹ ሁሉ የአብዮቱን ቸግሮች ሳይገባዊ በሆነ መንገድ መመርመርና ማስጨጥ ይገባቸዋል:: ዛሬ የኢትዮጵያ ተራማጆች የጊዜውን ሁኔታና የሰፊውን ሕዝብ ተግባሮች በተከከለ ካለጠቁ ነገ ለአብዮቱ መቀልበስ በታሪክ ፊት እንደሚጠየቁ መረዳት አለባቸው:: ተራማጆች የአንድን ተጨባጭ ሁኔታ ትንተና ሲያደርጉ ከሳይንሳዊ የአተናተን ዘዴ እንዳይርቁ መጠንቀቅ አለባቸው:: እንዳንድ ተራማጅ ነን ባዮች ለኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮት መፃኔት ሲያትቱ ከሚመኙት አንጻ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አይነሱም:: በዚህ በአብዮታችን አጭር ዕድሜ ገናና ተዋናይ የነበረቸው ኢህአፓ ከወዝአደሩና ከአርሶ አደሩ ውስጥ ተተፋቶ መውጣትና ወደ ተራ አሸባሪነት መለወጥ የሚያመለክተው ይህንኑ ነው:: ስለዚህ ተራማጆች ሁሉ በአጉል ጀብደኝነት በስሜታዊነትና ጥራዝ ነጠቅነት እንዳይጠቁ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው:: ሁለተኛ ደግሞ ጉዳት ከላይ ከተጠቀሰው ምንም የማያንስ ስለአብዮት፣ ስለትግል፣ ስለወዝአደሩ ፓርቲ አጣዳፊነት በዙ የሚያወራ ነገር ግን አድርባይነቱ የአብዮቱን መሠረታዊ ቸግሮች እንዳይጠቅምና ለዚያም እንዳይታገል ያገደው ያዋቂ አጥሪ አለ:: ተራማጆች ሁለተኛም ስህተቶች አዝማሚያዎች ማጋለጥና መታገል አለባቸው::

ከላይ ላነሳናቸው ጥያቄዎች የሚሰጡት መልሶችም ከተለያዩ መደቦች የተለያዩ መልሶችን እያገኙ ነው:: አድሃሪዎችና አናርኪስቶች በጠቅላላው ዛሬ የአብዮቱን ቸግሮች ያመጣው ደርግ ነው በማለት ያለ የሌለ ኃይላቸውን በፀረ ደርግ አመጽ ላይ ይጥላሉ:: አድርባዮችም "አናሸንፋለን" ፣ "አብዮቱ ገፍቷል" እያሉ የአብዮቱን ድክመቶች ሁሉ በተራማጆች ላይ ይጥላሉ:: ከዚህ ሁኔታም ለመውጣት በደፈናው መታገል ብቻ እንደሆነ ይናገራሉ::

የአብዮታችን ቸግሮች በርግጥ ከአብዮታችን መገፋት ጋር የተያያዙ ናቸው:: በዚህ ባጭር የአብዮታችን እድሜ መሃከል አብዮታዊ ተግባሮች ተከናውነዋል:: የፊውዳሉን ስርዓት የሚያናጋ የመሬት አዋጅ፣ የከተማ ትርፍ ቤቶች በመንግሥት

ቁጥጥር ስር መሆንና... ሌሎችም ለመዘርዘር የሚታክቱ አርምጃዎች ተወስደዋል:: ከነዚህ አርምጃዎች ጋርም የወደፊቱ ሕዝባዊ መንግሥት ጥንስስ ኃይል የሆኑ ሕዝባዊ ድርጅቶች እንደሀሸን ፈለተዋል::

በአብዮቱ ፈጣን ሂደት የተደፈጠጡና የተከረከሙ የቶሩ ምዱረ አድሃሪያን የፀረ አብዮት መፍጨርጨራቸው መበርታትና መቀነስ በየጊዜው ቢለያይም በተመቱ ቁጥር አሚን በለው የሰራውን ሕዝብ አርምጃ እንደ "ዕጋ" ተቀበለው አያውቁም::

አስከተወሰነ ደረጃም በተለይም የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትን ወላዋይነት በመጠቀም አብዮቱን በሰላማዊ መንገድ ለማኮላሸትና ባጭሩ ለመቀጨት ያለቆከሩት የለም:: በተለይ ደርግ ውስጥ በነበረ የኢዲዩ፣ የኢህአፓና የኢሕሰስ ወኪሎች አማካይነት በደርጉ ውስጥ ያሉ ተራማጆችንና በውጭም ያሉትን ተራማጆችና አገርወዳድ ዴሞክራቶች... ለመጨፍጨፍና አብዮቱን ለመቀልበስ በተደጋጋሚ ብዙ ሙከራዎች አድርገዋል:: በአብዮታችን የመጣው አንጋፋ ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ከማስፈራራት አንስቶ እስከተቀነባበረ ግልጽ ወረራ ድረስ የታቻለውን ለማድረግ ሞክሯል:: በመቀሳሰው አብዮታችን ፊውዳሊዝምን፣ ኢምፔሪያሊዝምን፣ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን ምንም ምቱ ቢለያይ እንደከረከማቸው አያጠራጥርም:: ዛሬ በአገራችን ላይ የተቃጣው ወረራ የሚያሳየን አንድ ነገር ቢኖር አብዮታችንና ያሳጠፋቸው ግን የሸነቆጣቸው ጠላቶቻችን ኃይላቸውን አስተባብረው መነሳታቸውን ነው::

በሰሜን ኢትዮጵያ የኤርትራ ተገንጣዮች በኢምፔሪያሊዝምና በአድሃሪ አገሮች ገፊነት ኤርትራን ለመገንጠል እየተሯሯጡ ናቸው:: ከታች በሰፊው የምንመለስባቸው ጥያቄዎች አስከሌ ተመለሱ ድረስ የኢትዮጵያ ጭቁኖች ኤርትራ ተገንጥላ ያድሃሪያዎች መፈንጫ ስትሆን የሚያዩበት ቀን ሩቅ አይሆንም:: የኢዲዩ ሰቻችም እንቅስቃሴ በቀላሉ የሚታይና የሚናቅ አይደለም:: በምስራቅና በደቡብም ዛሬ ሕዝባዊ ሠራዊቱና መደበኛው ሠራዊት በየሰዓቱ፣ በየደቂቃው፣ በየሴኮንዱ ህይወትን እየሰዋ ነው:: ዛሬ ሕዝባዊ ሠራዊት አስፈላጊውን ስንቅና አመራር በወቅቱ እንዲያገኝ ካልተደረገ በዚህ ግንባር በኩል የሚደረገው መስዋእትነት እንደሚበረከት ምንም ጥርጥር የለውም:: አብዮቱ ዛሬ ከፍተኛ አደጋ ላይ ይገኛል:: የኢትዮጵያ ብሄራዊ ክብርን፣ ህልውናን፣ አብዮቱ ትልቅ ፈተና ላይ ይገኛሉ!

ስለሆነም ጠላቶቻችን የተለያዩ ምት ተመተዋል:: ፊውዳሊዝም፣ ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ተከርክመዋል:: ነገር ግን ከነዚህ ሶስት ጠላቶቻችን ሁሉ በደንብ ያልተመታው ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ነው:: ከኃይለ ስላሴ የተወረሰው የፊውዳል ቢሮክራሲ ዛሬ ሲሻው ከደርግም በላይ የደርግ ወዳጅ



ሆኖ፣ ሲያሻው ደግሞ የደርጉን አድሃሪ ርዝራዦች ሁሉ አስተባብሮ የፀረ አብዮትን ሰፈር እየመራ ነው:: ዛሬም አብዮቱ ከውጭ ዘብ ሳለ ከውስጥ የቦርዷራነትን ሚና የሚመራው ይኸው ያረጀና ያፈጀው ቢሮክራሲ ነው:: ምንም እንኳን በሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጠላቶች ላይና በቢሮክራሲው በራሱ ላይ የተወሰደው አርምጃ የማይናቅ ቢሆንም አብዮቱን ለማራመድ በቢሮክራሲው ላይ ሊወሰድ ከሚገባውና ከሚቻለው አርምጃ አንፃር ስናየው በቢሮክራሲው ላይ የተወሰደው አርምጃ ኢምንት ነው:: በየጊዜው ለሕዝባዊ ድርጅቶች ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፣ በቢሮክራሲው ትእዛዝና አሻጥር የሕዝባዊ ድርጅቶች መሪዎች ይታሰራሉ፣ ይገደላሉ፣ ሕዝባዊ ድርጅቶች ይፈርሳሉ::...

እንደሚታወቀው ወዛደሩ የአብዮቱ መሪ መደብ ነው:: ወዛደሩ ምንም እንኳን እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በኢህአፓ ጀሌዎች ተወናብዶ እንደነበረ ቢታይም ዛሬ ወዛደሩ እሱን መስለው በተጠጉት ጠላቶች ላይ ነቅቶባቸዋል::

የኢህአፓን ቅጥር ነፍሰ ገዳዮችና አድሃሪያዎችን እየመነጠረ መጥቷል:: በተለይ አብዮታችን ወደአጥቂነት ከተሸጋገረበት ወዲህ መሰረ ወደተከላካይነት እስከተመለሰበት ድረስ ወዛደሩ ጓቢንሊን በተመሳሳይ አሠራር አድሃሪያዎች ላይ የወሰደው ቆራጥና የማያወላውል አርምጃ ከገንገድ አደርባዮች በስተቀር ማንም እንደማይክደው የታወቀ ነው:: ባለፈው ዓመት ብቻ ወዛደሩ "ታጋይ በሞት ትግሉ አይቆምም" እያለ ስንትና ስንት ጓዶቹን እንደሰዋ ተራማጆች ሁሉ የሚያስታውሱት ነው::

የወዛደሩ የዓመቱ ታላቅ ድል ባድሃሪውና ባናርኪስቱ ኢሠአማ መያዝር ላይ የነገሰው የወዛደሩ ቤት መኢሠማ ነበር:: የመኢሠማ መቋቋም ለአብዮታዊያን ታላቅ ድል የነበረውን ያህል ለፀረ አብዮታዊያን ደግሞ በቀላሉ የማይሽር ቁስል ያተረፈላቸው ምት ነበር::

ባለፈው ዓመት ብቻ እንኳን ወዛደሩ ሁለት ረጋዪ ጓዶቹን በተከታታይ አጥቷል:: በመጀመሪያ የመጀመሪያው የመኢሠማው ሊቀ መንበር ጓድ ቴዎድሮስ በቀለ፣ ቀጥሎም ሁለተኛው ሊቀ መንበር ጓድ ተመስገን ማዴቦ አጥቷል::

እነዚህ ሁለት ጓዶች ለአብዮታችን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ የወዛደሩ መሪዎች ናቸው:: ሁለቱም መኢሠማን በደማቸው የኖሩ ናቸው:: ሁለቱም ለአደሉ፣ ለታጋዩና ለረራማች መኢሠማ መሠረት የሰኩላቸውን ደም ያፈሱ ናቸው:: ሁለቱም ለረጅም ዘመን በትእሰቱ ከበርቴዎች ሲረገጥ ለነበረው ወዛደር ነፃነት የሞቱ ናቸው::

ወዝአደሩ ገና የቴዎድሮስ በቀለን ሀዘን ሳይወጣው፣ የጓድ ቴዎድሮስ የፈሰሰ ደም ሳይደርቅ፣ በጓድ ቴዎድሮስና በሌሎች የመኢሠማ ጓዶች ላይ የተሰነዘረው ፀረ አብዮት በትር አያበለሰለሰው ባለ በታላቅ ድፍረት እንደገና ሌላ ዱላ ተቃጣበታል:: ወዝአደሩ ይህንን ሁሉ ግፍና ደባ በትዕግስት አልፎታል::

አድሃሪያኖች ሁሉ ዛሬ የወዝአደሩን ትእግስት እንደ ፍርሃት የቆጠሩት ይመስላል:: ወዝአደሩ ታጋሽ መደብ ነው:: በጫንቃው ላይ ለረጅም ዘመን ግፍና በደል ተሸክሟል:: ግን ይህን ግፍና በደል አንድ ቀን አሽቀንጥሮ ይጥላል:: ከመጨረሻው ወሳኝ ቀን በፊትም በተለያዩ እርምጃዎች ለፀረ አብዮት ክንዱን ያሳየዋል::

ዛሬ አብዮቱ ትልቅ አደጋ ላይ በሚገኝበት ወቅት መንግሥትም /ከሰፊው ሕዝብ ጐን ነኝ ካለ/ ተራማጆችም፣ አገርወዳዶችም፣... ሁሉ ሃላፊነት አለባቸው:: በተለይ ዛሬ የተቀሰቀሰውን የወዝአደሩን ቁጣ መኢሠማ አስተባብሮ የመምራት ሃላፊነት አለበት::

አብዮታችን የሰፊው ሕዝብ ድጋፍ አልጐደለውም:: ለዘማቹ ስንቅ አቅርቧል፣ ደም ለግሷል፣ ፀረ አብዮተኞችን አጋልጧል... የጐደለው ነገር ቢኖር አብዮታዊ አመራር ብቻ ነው:: ዛሬ በየቦታው እንደቅጠል ለሚረግፉት ጓዶቻችን ደም፣ ለብሄራዊ ክብራችንና ህልውናችን መደፈር፣ ለውዷ አገራችን የጠላት መፈንጫ አውድማ መሆን ተጠያቂው አድሃሪ ቢሮክራሲ ነው:: ለነፃ እርምጃዎች መታገድ፣ ለተራማጆች መንገላታት፣ በጠቅላላው ለውጥረት ተጠያቂው ቢሮክራሲው ነው::

አብዮቱ በርግጥ ከገባበት ማጥ እንዲወጣና ወደፊት በአዲስ ኃይል እንዲራመድ የሚፈልጉ ሁሉ ቢሮክራሲው እንዲመታ፣ ዘመቻው አብዮታዊ አመራር እንዲኖረው... እና ዝርዝር ለእነዚህ ጥያቄዎች መፍትሔ መንገድ ለሚከፍቱ የዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ መለቀቅ መታገል አለባቸው:: አንድ ገጣሚ እንዳቀረበው ወዝአደሩ ዛሬ — እያ ዛሬ

ነፃ እርምጃ — ነፃ እርምጃ
መርናለ ትግለ አይቆምም ታጋይ እንጂ በሉ ማጓራት
መፈክር አዝሎ መጉተት
ጊዜ እንዳለው ሰሞኑን
እንደጠቆሙ ሃቁን
እኔም እንደቦቴ እስትንፋሴ ይኸው ነው
ዲሞክራሲ ለጭቁኖች ያለገደብ በቶ እምጠነው
ያናርኪ ሀታ፣ የቀለበሽ ዱላ ወርቅ ነው
“እምፏለሁ” የምለው ለዚህ ነው::
ጓዶች... ሰቄን፣ ቁስሌን፣ ረሃቤን እፎሰን
የቀለበሽ ቢሮ በካቦን አንገፈገፈኝ::
ነው የሚለው::



ስለዚህ ከተለያዩ ድርጅቶች የተውጣጣን ወዝአደሮች ይህን ብሶታችንን መኢሠማ ሰምቶ በተቀነባበረ መንገድ ከሥራ እንዲያውለው እንጠይቃለን:: መኢሠማም ሆነ መንግሥት በአጣዳፊ እርምጃ ካልወሰደ ግን አዲስ አበባን በአድሃሪያን ደም ልናጥለቀልቃት፣ በቢሮክራቶቹ፣ ከጥገት ርስታቸው ሸሽተው አዲስ አበባ በየመንደሩ በሚደለቱ የጥገት የመሬት ከበርቴዎች፣ በተፈታ ቅጥር ነፍሰገዳዮች፣ በጠቅላላው ምድረ አድሃሪያን ላይ ሽብር ልንነዛ መነሳታችንን እንገነዘባለን:: ጠላቶቻችን ይህን “መርዶ” ወዳጆቻችንም ይህንን የምስራች ከአገር አገር፣ ከአጥናፍ እስከአጥናፍ እንዲያስተጋቡ እንጠይቃለን:: ጥያቄዎቻችን የጥቂት ግለሰቦች ሁካታ ነው ከተባለ የጥቂት ግለሰቦች ሁካታ ሳይሆን የሰፊው ወዝአደር ብሶት እንደሆነ በገቢር እናሳያለን::

<u>ጥያቄዎቻችን</u>

1 — ሕዝቡን ይበልጥ አንቀሳቅሶ አብዮትን ለማራመድ የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኑ ያለገደብ እንዲለቀቁ፣

2 — አብዮታዊ ዘመቻ በቢሮክራሲው አዝማችነት ድል ሊመታ ስለማይችል አብዮታዊ ካድሬዎች፣ ዘማች ወዝአደሮች፣ አርሶአደሮችና ሌሎችም ተራማጆች በየደረጃው የሚሳተፉበት አብዮታዊ አመራር በአፋጣኝ እንዲመሠረት፣

3 — አብዮታችንን ለመቀልበስ የፀረ አብዮት ሰፈር አስተባባሪ መሪ ቢሮክራሲው እንዲመታ፣ በቀንደኛ አድሃሪ ቢሮክራቶች ላይ አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድ፣

4 — በሕዝባዊ ድርጅቶች ላይ የሚፈጸመው ማስፈራራትና ተጽእኖ እንዲወገድ መንግሥት በተቀነባበረና ዲሲፕሊን በተሞላው መንገድ ነፃ እርምጃ እንዲወስዱ እንዲፈቅድ፣

5 — ሰልጥነው ለሚጠባበቁ የነቁ ወዝአደሮች ካለአንዳች መበላለጥ ትጥቅ ባስቸኳይ እንዲሰጥ፣

6 — አድሃሪ የደርግ አባሎች እንዲጋለጡና ቆራጥ አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው፣

7 — ሰፊውን ሕዝብ ወደር በሌለው ሁኔታ ሲያነቃ ሲያደራጅ የነበረ ሃቀኛ ተራማጆች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመታሰርና በመሰደድ ላይ ስላሉ ይህ አድራጎት ፀረ ሶሻሊስት በመሆኑ የታሰሩት ባስቸኳይ እንዲለቀቁ፣ በቀሩትም ላይ የሚደረገው የቀን ከንፍች አፈናና ክትትል እንዲቆም፣

8 — የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምን በአስቸኳይ በሥራ መተርጎም በተለይም ዛሬ የአብዮታችን አንገብጋቢ ጥያቄዎች የሆኑትን የብሄረሰቦች እኩልነትን መብት ማወቅ፣ ማለትም ለያንዳንዱ ብሄረሰብ ተጨባጭ ችግር እንደየሁኔታው ተጨባጭ መፍትሄ ደረጃ በደረጃ መስጠት፣ እንዲሁም ለምናካሄደው አብዮታዊ ጦርነት ከሁሉም የበለጠ በራሳችን መተማመን፣

9 — ከቢሮክራሲው ቁጥጥር ነፃ የሆነ በሕዝባዊ ድርጅቶች ትብብርና ቅንብር የሚመራ የመመንጠር ዘመቻ በአስቸኳይ በአድሃሪያንና በቅጥር ነፍሰ

ገዳዮች ላይ እንዲደረግ፤

10 — በአድሃሪው የቢሮክራሲ አሻጥር የታሰሩና በመታሰር በመሰደድ ላይ ያሉ የቀበሌ ማህበራት ሠራተኞች፣ የወዛደር መሪዎች፣ የአብዮት ጥበቃ ጓዶች፣ ተራማጅ የወጣት ማህበራት መሪዎች፣ የጭቁን ብዙሃን ታጋይ ተራማጆችና ሃቀኛ ተራማጅ ምሁራን በአስቸኳይ እንዲፈቱና ክትትሉም እንዲቆም፤

11 — አድሃሪው ቢሮክራሲ የታወቀት ቁጥር ነፍሰገዳዮችን በሰበብ አስባቡ ከእስር ቤት መፍታትና መልሶም የሰፊውን ሕዝብ ማስጨፍጨፉ በአስቸኳይ እንዲቆም፤

12 — መኢሶን በጓድ ተመስገን ማዲቦ ሞት ምክንያት ያቀረበለትን አቤቱታዊ ጥሪ በሙሉ ልብ የተቀበለ ነው በለሆነ በሥራ ለመተርጐም መንግሥትን ትብብር እንጠይቃለን::

የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኑ አሁኑኑ !

አድሃሪው ቢሮክራሲ ይመታ !

ፊውዳሊዝም፣ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ይውደሙ!!

የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ የሕዝብ አመጽ ያሸንፋል !!

ግልባጭ

— ለ8 የኢንዱስትሪ ማህበራት
— ለአ.አ. አካባቢ የገበሬ ማህበራት
— ለአ.አ. ከተማ ነዋሪዎች አጠቃላይ ምክር ቤት
— ለ25ቱ የከፍተኛ የከተማ ነዋሪዎች ማህበራት
— በቀበሌ ማህበራት ስር የተደራጁ የወጣቶች ማህበራት
— " " " " የሴቶች "
— ለለቀ ለደ የወዛ አደር ድርጅት ማህበራት
— የአብዮታችው ወደ ተከላካይነት ማሽቆልቆል ለሚያንገበግባቸው ታጋዮች ሁሉ !

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board

## ማሳሰቢያ

ውድ አንባቢያችን

የውጪን ጎዳና ቱ ከውስጥ ሆኖ ቦርቦሮ ለማዳከም ያደረገው ሙከራ በሳል ተካካለት እርሱን ከጎቱና ቲያችን ያገለለው ፀረ ሕዝብ ቡድን ካቀረበ ጋዜ ጀምሮ፣ከአስር ዓመት በላይ ሰፊው ሕዝብ ጉን በመሰለፍ ያለማቋረጥ ያለመታከት ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳሊስት ትግል ሲያካሂድ በኖረው ማህበራችን በነዚህም አስር ዓመታት ያስተጠማመውን ነፃነት በመንጠቅ የሰፊውን ሕዝብ ድምፅና ትግል ሲያስተጋባ በኖረት ቻከ የተናወጸ የተማሪ ማህበራት መጽሔት በላይ የሰፊው ሕዝብ ማስተማሪያና መስተናገኛ ሆኖ በቆየት በ<u>ታጠቂና</u> በ<u>ትግላችን</u> ስም መጠቀም ጀምረዋል:: የዚህ ፀረ ሕዝብ ቡድን ዓላማ ማህበራችን እንዲሁም <u>ታጠቂና</u> <u>ትግላችን</u> በአስር ዓመት ቀራኒ ትግል ያተረፈት ስም ተጠቅሞ ፀረ ሕዝብ ፖለቲካውን ለመሸረን ነው::እንዲሁም ከውስጥ ሆኖ ያታለውን የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ተራማጆች አንድነት የማፍረስ ሙከራ ከውጭ ሆኖ ለማከናወን በመጎዝት ለማፋፋም ነው::ይህም እንደሚባክ የተረጋገጠ ነው:: ለማንኛውም፣የተለመደው መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ አድራሻ/ማለትም P.O.BOX 3198 10364 STOCKHOLM - SWEDEN ያለ ያነኛ የዓለም ቦቱ የኢትዮጵያ ተማሪዎች <u>ማህበር</u> አባላትን የሚያመለከተ ገን የማህበራችን መጽሄቶች ስም የያዙ መጽሄቶች ወዘተ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር መጽሄቶች አለመሆናቸውን እንደታወቁልንና እንዲታወቁልን እንመኛለን::ለእነዚህ አይነት መጽሄቶች ተመያዘው ''ዓለም ዓቀፍ ፊንፊኔ'' በሚባል ስም የታወቀው የነ አቦለዐበን — መንገሻ ሥዩም የወጣቶች ድርጅት ነው::

ከፋፋዮችና አወናባጆች ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ይውደሙ!
የእውነተኛ አብዮታዊያንና ተራማጆች አንድነት ይኑር!
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው!

በአኢተማ መጽሄት አዘጋጅ ቦርድ